


CamScanner

# ድ ር ሳ ነ   መ ስ ቀ ል

በአማርኛ

## ምዕራፍ አንድ

፩ አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን የክብር ባለቤት የሆነ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል የድርሳኑን መጽሐፍ ለመጻፍ እንጀምራለን፤ የእግዚአብሔር አብም ፍቅር ሰላም በከበረ መስቀሉም የሚገኝ ባለሟልነት በእውነት ለዘላለሙ በላያችን ይደር አሜን።

፪ የዓለም መድኃኒት የክብር ባለቤት ጌታ ክርስቶስ ስለተሰቀለበት ዕፀ መስቀሉ ከተቀበረበት ከጎልጎታ ጉድጓድ እንዴት እንደወጣ ይህን ድርሳን የደረሰውና የጻፈው የቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ አባ መቃርዮስ ነው።

፫ ዐመፅን ክፋትንና ቅናትን የተመሉ አይሁድ ከቀበሩት በኋላ በሦስት መቶ ዓመት ጥልቅ ከሆነ ከመቃብር ጉድጓድ ይህን የከበረ መስቀል ያወጣው ማን እንደሆነ።

፬ የዚህንም በእግዚብሔር ልጅ በጌታ ክርስቶስ ደም የከበረ መስቀል ድርሳኑንና ቃል ኪዳኑን ሁሉ መሲሐውያን ወንጌላውያን ለሆን ለሁላችን ለክርስቲያን ወገኖች የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ አባ መቃርዮስ ነገሮናልና ለርሱም ለጌታ በዕውነት ለዘላለሙ ክብር ምስጋና ይሁን አሜን።



CamScanner

# ድ ር ሳ ነ  መ ስ ቀ ል

በአማርኛ

## ምዕራፍ ሁለት

፩ እነሆ ይህ አባት የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ አባ መቃርዮስ እንዲህ አለ የክብር ባለቤት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የከበረ መስቀሉ በንግሥት ዕሌኒ ትእዛዝ ጥልቅ ከሆነ ከጎሎጎታ ጉድጓድ አስደናቂ በሆነ ታላቅ ተአምር እንደወጣ እነግራችኋለሁ፡፡

፪ ዳግመኛም ዓለምን ለማዳን ስለ ብዙዎች ቤዛነት የክብር ባለቤት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተሰቀለበት ዕፀ መስቀል የድርሰት ዜናውንና የቃል ኪዳኑን ሀብት እነግራችኋለሁ አለ፡፡

፫ ዐመፅንና ቅናትን የተመሉ ክፉዎች አይሁድ በርሱ የሚደረጉትን ብዙዎች አስደናቂዎች ተአምራቶችን በአዩ ጊዜ የሥልጣኑና የተአምራቱ ኃይል ቃል ኪዳኑም እንዳይገለጽና እንዳይታወቅ የከበረ መስቀሉን እነሆ ጥልቅ በሆነ ጉድጓድ ውስጥ ቀበሩት፡፡

፬ ዳግመኛ አባ መቃርዮስ እንዲህ አለ በኋላ ዘመን በሺህ አርባ አራት ዓመት የዓለም መድኃኒት ለተሰቀለበት መስቀልና ለእመቤታችን በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ለጸናች ቅድስት.ማርያም ወዳጆች በሆኑ በዳግማዊ ዳዊትና በልጁ በዘርዐ ያዕቆብ በመንግሥታቸው ወራት ወደ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ይሔድ ዘንድ እንዳለው የዚህን የከበረ መስቀል ምሥጢሩን እነግራችኋለሁ አለ፡፡

# ድ ር ሳ ን መ ስ ቀ ል

በአማርኛ

## ምዕራፍ ሁለት

፩ እነርሱም የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመኝታቸው በሕልም መስቀሌን በመስቀል ላይ አኑሩ በአላቸው ጊዜ በኢትዮጵያ ሀገር ያኖሩታል።

፪ ስለዚህም ይህ መስቀል በኢትዮጵያ አድባራት ሲዞር ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ይኖራል፣ ከዚህም በኋላ ወደ ደብረ ከርቤ ይወጣል።

፫ ይቺም ቦታ አስቀድሞ ደብረ ነገሥት ትባል ነበር፣ ደግሞ ሁለተኛ ደብረ ነጎድጓድ ሦስተኛ ደብረ ከርቤ ተብላለች፣ ሰሎሞን በመሐልየ እንግዲህ እኔ ራሴ ወደ ደብረ ከርቤ እሔዳለሁ እንዳለ፡

፬ ዳግመኛ ደብረ ከርቤ ያለው የክብር ባለቤት ጌታ ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕለት ዓርብ ነው።

፭ ሁለተኛም ከርቤ ማለት መድኃኒታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የተቀበለውን መከራ ማሰብ ነው። ሦስተኛም ይች ቦታ ደብረ ከርቤ የተባለችው የክብር ባለቤት የሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀሉ በውስጥዋ ስለሚኖር ነው።

፮ ይቺም ቦታ በኢትዮጵያ ከአሉ ገዳማት ሁሉ ከአድባራትም ሁሉ ከቦታዎችም ከሀገሮችም ሁሉ ከፍ ከፍ ያለች ናት።

# ድ ር ሳ ነ  መ ስ ቀ ል

በአማርኛ

## ምዕራፍ ሁለት

፲፩ ይህ የከበረ መስቀል ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሲዞር የኖረ ማረፊያ አጥቶ ወይም የደብረ ከርቤን ቦታ ባለማወቁ አይደለም፤ ከቅድስት ድንግል እናቱ እመቤታችን ማርያም ጋር የክብር ባለቤት መድኃኒታችን ክርስቶስ በስደቱ ወራት በእግሮቹ መመላለስ የግብጽ ምድርና የኢትዮጵያ ሀገሮች እንደተቀደሱ ደግሞ በስብከቱ ወራት የመንግሥቱን ወንጌል እያስተማረ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሦስት ዓመት ከሦስት ወር እንደተመላለሰ፣ እንዲሁም የክብር ባለቤት የሆነ የጌታ ክርስቶስ መስቀል ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በኢትዮጵያ ሀገር ውስጥ ተመላለሰ።

፲፪ ነጻነት ያላት የተቀደሰች ሀገር የኢትዮጵያ ገዳማቶቿ፣ አጸዶቿ፣ ቦታዎቿ፣ ተራራዎቿ ይከብሩ ዘንድ ነው።

፲፫ ይልቁንም ደብረ ከርቤ ትከብር ዘንድ ነው።

፲፬ ይቺም ደብረ ከርቤ ሁለመናዋ የመስቀል አምሳል ነው፣ ከእርሷም ጥበብን ዕውቀትን የሚገልጽ መንፈስ ቅዱስ እስከ ዓለም ፍጻሜ አይለይም አይርቅም፣ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ዓለም ለማሳለፍ በግርማ መንግሥት እስከሚመጣ ድረስ አይለይም ለርሱም ከብር ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን።



CS CamScanner

# ድ ር ሳ ነ  መ ስ ቀ ል

በአማርኛ

## አንደኛ ተአምር

ይቅርታው ምሕረቱ ከባሪያው ከገብረ መድኅን ጋር ለዘላለሙ ይሁንና ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡፡

፩ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋችንን ለብሶ በምድር ላይ በተገለጠ ጊዜ ሰው ሁኖ ሊሠራው የሚገባውን ሁሉ ሠርቶ ፈጽሞ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀምጦ እንዲህ አላቸው እኔ የሞት ፈጣሪው ስሆን ሰውነቴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች፡፡ ይህንንም ብሎ በወዳጁ አልዓዛር ቤት ለራት ማዕድ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ፡፡

፪ ሐዋርያትንም ከእናንተ አንዱ በጠላቶቼ አይሁድ እጅ አሳልፎ ይሰጠኛል አላቸው፤ እነርሱም እርስ በርሳቸው ተያዩ አቤቱ እኔ እሆን እንጃ ወይም ሌላ አሳልፎ የሚሰጥህ አለ አሉት፡፡

# ድ ር ሳ ነ መ ስ ቀ ል

በአማርኛ

## አንደኛ ተአምር

ጌታችንም ወደ እኔ ወጭት እጁን የሚሰድ የሚያሲዘኝ እሱ ነው አላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ይሁዳ እጁን ወደ ወጭቱ ጨመረ ወዲያውኑ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ ከዚያ እንጀራ ጋር ሰይጣን ገባ፡፡ ይቅርታው ምሕረቱ ከእኛ ጋር ይሁን፡፡ ለዘላለሙ አሜን፡፡

## ሁለተኛ ተአምር

ይቅርታው ምሕረቱ ከባሪያው ነፍስ ከገብረ መድኅን ጋር በዕውነት ለዘላለሙ ይኑርና ጌታችን ፈጣሪያችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡፡

፩ አይሁድም የቀራንዮ ሰው ስምዖንን መለሱት ያንንም ዕፅ አሸከሙትና ከከተማ ውጪ ወዳለች ጎልጎታ ወደምትባል የአትክልት ቦታ ሔዱ በዚያም የእግዚአብሔር መልአክ የቀበረው የአዳም መቃብር አለ ነቢይ በምድር መካከል ድኅነትን አደረገ ያለው ይፈጸም ዘንድ በምድር መካከል በዚያ የከበረዕፀ መስቀልን ተከሉ፡፡



ሥዕል 4፦ ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤልን አንገቱን በሰይፍ እንደቀሉት፤

## ገድል ዘቅዱስ ናትናኤል

፩. በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ ሥሉስ አጎዜ ኵሉ ዓለም መሐሪ ወመስተሣህል ስብከቱ ለቅዱስ ወብፁዕ ስምዖን ወልደ ቀለዮጳ ዘተሰምየ ይሁዳ ዘበትርጓሜሁ ናትናኤል ዘይሰመይ ቀናዔ። ወኮነ ኤጲስ ቆጶሰ በኢየሩሳሌም እምድኅረ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላመ እግዚአብሔር አሜን።

፪. ወኮነ ጊዜ ተጋብኦቶሙ ለሐዋርያት ቅዱሳን ኀበ ደብረ ዘይት ከመ ይትካፈሉ አህጉረ ዓለም። ወእንዘ ይጼልዩ ወይባርክዎ ለእግዚአ ብሔር መጽአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት፤ ወቆመ ማዕከሎሙ። ወይቤሎሙ ሰላመ አቡየ ይኅድር ላዕሌክሙ ኦ አርድእትየ ቅዱሳን ወውእቶሙኒ ተዓፀዉ። ወወፅአ ለይሁዳ ከመ ይሑር ብሔረ ሰማርያ ወይስብክ ባቲ ወንጌለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። ወአውሥአ ስምዖን ወይቤሎ ለእግዚእነ ኩን ምስሌየ ኀበ ኵሉ መካን ዘአሐውር ባቲ ወንሕነ ንትዔገሥ ኵሎ ምንዳቤያተ ዘይመጽእ ላዕሌነ ዳዕሙ ይሑር ምስሌየ አቡየ ጴጥሮስ ያብጽሐኒ እስከ ምድረ ሰማርያ።

፫. ወይቤሎ እግዚእነ ለጴጥሮስ ከመ ይፃእ ኀበ ሀገረ ሮምያ። ዳዕሙ ውእቱ ይበጽሕ ኀቤከ እስከ ያበጽሐከ በሰላም። ወእምኅረዝ ፈጺመከ ስብከተከ ወዜናከ አንተ ትገብእ ኀበ ኢየሩሳሌም እምድኅረ ሞቱ ለያዕቆብ ጻድቅ ወትሠየም ባቲ ኤጲስ ቆጶሰ እምድኅሬሁ ወአንተ ትፈጽም ገድለከ። በከመ ፈጸመ ያዕቆብ ጻድቅ በውስተ መካን ናሁ እምይእዜ ኦ ኅሩይየ ስምዖን ፃእ በሰላም ኃይለ አቡየ ይርዳዕከ። ወባረከ እግዚእነ ላዕሌሁ ለውእቱ ወለኵሎሙ ሐዋርያት፤ ወዐርገ ውስተ ሰማያት በዓቢይ ስብሐት።

## የቅዱስ ናትናኤል ገድል

1. ሦስት በሚሆን ዓለምን በያዘ፣ ፈጽሞ ይቅር በሚል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ብፁዕ የሚሆን ይሁዳ የተባለ የቀለዮጳ ልጅ የቅዱስ ስምዖን ስብከት ይህ ነው። ትርጓሜውም ቀናተኛ የተባለ ናትናኤል ነው። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ከያዕቆብ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ ነበር ለዘለዓለሙ አሜን።

2. የዓለም ሀገሮችን ይካፈሉ ዘንድም የቅዱሳን ሐዋርያት መሰብሰብ በደብረ ዘይት ተደረገ። ሲጸልዩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑም ምስጋና ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ። በመካከላቸውም ቆመ። የተቀደሳችሁ ደቀ መዛሙርቶቼ ሆይ የአባቴ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን አላቸው። እነርሱ ዕጣ ተጣጣሉ። ወደሰማርያ እንዲሄድና ምስጋና ይግባውና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ያስተምር ዘንድ ለይሁዳ ወጣ፤ ስምዖንም መለሰ። ጌታችንንም በምሄድባት ሁሉ ከእኔ ጋር ሁን። እኛም በእኛ ላይ የሚመጣውን መከራ ሁሉ እንታገሣለን። ነገር ግን አባቴ ጴጥሮስ እስከ ሠርያ ያደርሰኝ ዘንድ ወደ እኔ ይሂድ አለው።

3. ጌታችንም ጴጥሮስን ወደሮም እንዲወጣ ነገረው። ነገር ግን እርሱም በሰላም እስከሚ ያደርስህ ድረስ ወደ አንተ ይመጣል። ስብከትህን ትምህርትን አስተምረህ ከፈጸምህ በኋላ ጻድቁ ያዕቆብም ከሞተ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ትመለ ሳለህ። ከእርሱ በኋላም ኤጲስ ቆጶስነት ትሾማለህ። ጻድቁ ያዕቆብ ተጋድሎውን እንደፈጸመ ገድልህንም ትፈጽማለህ። የመረጥሁህ ስምዖን ሆይ አሁንም በሰላም ሂድ፤ የአባቴ እርዳታ ያግዝህ አለው፤ ጌታችንም በእርሱና በሐዋርያት ላይ ባረከ። በታላቅ ምስጋናም ወደ ሰማይ ዐረገ።

፬. ወተንሥአ ስምዖን ወጸለየ ወበጽሐ ኀበ ኢየሩሳሌም ወጴጥሮስ ምስሌሁ አቅደመ ሐዊረ ኀበ ሰማርያ፤ ወሰበከ በዜና ወንጌል። ወስምዖን ሐዋርያ ሖረ ኀበ ቤተ ጉባዔሆሙ ወሰበከ ሎሙ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። ወሶበ ሰምዑ አይሁድ እለ ይነብሩ ውስተ ውእቱ መካን ቆሙ ላዕሌሁ ወዘበጥዎ ዓቢየ ወሰሐብዎ አፍአ ሀገር። ወተመይጠ ጴጥሮስ ወወፅአ እምኔሁ።

፭. ወስምዖንኒ ዓዲ ገብዓ ኀቤሆሙ ወቆመ ማዕከሎሙ ለጉባዔን፤ ወነበረ ኀቤሆሙ ፫ተ ዕለተ እንዘ ይሰብክ በስሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወአልቦ ዕደው እለ ኢየአምኑ በእግዚእነ ወበተፍጻሜተ ዕለት ሣልሲት ደወየ ወልዱ ለቀሲስ ዘስሙ ያዕቆብ ወሞተ፤ ወብእሲቱኒ እምእለ አምኑ በእግዚእነ በሀገረ ስምዖን፤ በጽሐ ኀበ አቡሁ ለወሬዛ ዘሞተ። ወይቤሎ ናሁ ሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ዝየ ሀሎ ጸውዖ ይጸሊ ላዕሌሁ ለወሬዛ።

፮. ወሖረ ውእቱ ብእሲ ፍጡነ ወጸውዖ ለሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። ወበጽሐ በፍሥሐ ወቆመ ላዕለ ወሬዛ ዘሞተ። ወይቤሎ ተአመንሁ በዘሰቀልዎ በወልደ እግዚአብሔር ወበዝ ትሬኢ ስብሐተ እግዚአብሔር ወይቤሎ አቡሁ ለወሬዛ ዘሞተ እመ ተንሥአ ወልድየ እሙታን ወለእመ እኔጽሮ ሕያዎ አአምን በክርስቶስ ዘተሰቅለ ከመ ውእቱ ወልደእግዚአብሔር ሕያው።

፯. ወሐዋርያሰ ሜጠ ገጾ ወጸለየ እንዘ ይብል እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ዘተሰቅለ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ እንተ አስተዳሎከኒ ለውእቱ ግብር ከመ እሰብክ በስምከ ቅዱስ ወቡሩክ ወሐመምከ በእንቲአነ ከመ ትቤዝወነ እምእደ ጸላዒነ፤ ወይእዜኒ ነጽር ኀበ ዝንቱ ወሬዛ ዘሞተ በሥምረትከ አዝዝ ከመ

4.ስምዖንም ተነሥቶ ጸለየ፣ ኢየሩሳሌምም ደረሰ። ጴጥሮስም አስቀድሞ ከእርሱ ጋር ወደ ሰማርያ ሄደ። የወንጌልን የምሥራችም አስተማረ። ሐዋርያው ስምዖንም ወደተሰበሰቡበት ሄደ። ምስጋና ይግባውና ስለጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም አስተማረ። በዚያ ቦታ የሚኖሩ ሰዎች በሰሙ ጊዜም በእርሱ ላይ ተነሡ። ጽኑ ድብደባን ደበደቡት። ወደ ከተማው ውጭም ጐተቱት። ጴጥሮስም ተመለሰ። ከእርሱም ወጣ /ተለየ/።

5. ዳግመኛም ስምዖን ወደ እነርሱ ተመለሰ። በተሰበሰቡት መካከልም ቆመ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እያስተማረም ለሦስት ቀን ቆዬ። በጌታችን የሚያምኑ ወንዶችም አልነበሩ። በሦስተኛው ቀን መጨረሻም ያዕቆብ የተባለ የአገልጋዩ ልጅ ታመመና ሞተ። ሚስቱም በስምዖን ሀገር ከአመኑ ሰዎች ወገን ናት። ወደሞተው ጐልማሳ አባትም ደረሰ። ምስጋና ይግባውና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው እነሆ ከዚህ አለ። ለጐልማሳው ይጸልዩለት ዘንድ ጥራው አለው።

6. ያም ሰው ፈጥኖ ሄደ። ምስጋና ይግባውና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሐዋርያም ጠራው። በደስታ ደረሰ። ከሞተው ጐልማሳ አጠገብም ቆመ። በሰቀሉት በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን አለው። በዚህም የእግዚብሔርን ክብር ታያለህ አለው። አባቱም የሞተው ልጄ ሕያው ሁኖ ከተነሣ ድኖም ካየሁት የተሰቀለው እርሱ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ።

7. ሐዋርያውም ምስጋና ይግባውና በጰንጤ ናዊው በጲላጦስ ፊት የተሰቀልህ በተቀደሰው በተባረከው ስምህ እንዳስተምር ለዚህ ተግባር የመረጥኸኝ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እያለ ፊቱን መልሶ ጸለየ። ከጠላታችን እጅ ታድነን ዘንድ ስለ እኛ ታመምህ። ዛሬም በፈቃድህ ወደሞተው ወደዚህ ጐልማሳ ተመልከት። ይነሣና ስምህን ያመሰግን ዘንድም እዘዝ፤ በዚህች ሀገር





CS CamScanner

ይትነሣእ ወይሰብሕ ስመከ ዮም እስመ በቅድመ እሉ ሕዝብ በውስተ ዛቲ ሀገር ከመ ይእመኑ በስምከ ቅዱስ።

፰. ወሶበ ይቤ ስምዖን ሐዋርያ ቡሩክ ዘንተ ሜጠ ገጾ ኀበ መካን ዘሀለወ ቦቱ ወሬዛ። ወይቤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ተንሥእ ወቁም ይርአዩከ ሕያወ። ከመ ኵሎሙ እለ ተጋብኡ ይእመኑ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት፤ ወበይእቲ ሰዓት ተከሥተ አዕይንቲሁ ለውእቱ ወሬዛ ወተንሥአ። ወሖረ ወአዘዘ ከመ ያምጽኡ ሎቱ ዘይበልእ።

፱. ወሶበ ርእዩ ጉቡዓን ዘንተ መንክረ ቀርቡ ኵሎሙ ወሰገዱ ውስተ ምድር ለሐዋርያ፤ ወአምኑ ኵሎሙ በእግዚአብሔር ወይቤሎሙ ውእቱ ፩ዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላከ ስምዖን ሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት ከመ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው። ወአቡሁ ለውእቱ ወሬዛ አምነ ወኵሎሙ ሰገዱ ታሕተ እገሪሁ ለቅዱስ ሐዋርያ። ወይቤልዎ ኦ እግዚኦ በምንትኑ ንድኅን። ወይቤሎሙ እመኑ በኵሉ አልባቢክሙ አንትሙ ወትድኅኑ።

፲. ወውእቱኒ መሀሮሙ መጻሕፍተ ቅዱሳተ። ወአጥመቆሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ሀገር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። ወወሀቦሙ ምሥጢራተ ቅድሳት፤ ወአዘዞሙ ይሕንፁ አብያተ ክርስቲያናት። ወሤመ ሎሙ ኤጲስ ቆጶሰ ዘኮነ ሊቀ ጉቡዓን ዘስሙ ቆርነሌዎስ። ወሤመ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ፤ ወወሀቦሙ ወንጌለ ቅዱሰ። ወነበረ ኀቤሆሙ ፴ መዋዕለ እንዘ ይሜህሮሙ ሕገ እግዚአብሔር። ወእምድኅረዝ ገብአ ኀበኢየሩሳሌም።

፲፩. ወሶበ ቀተልዎ አይሁድ ለቅዱስ ያዕቆብ። ወአርድእትኒ ኮኑ ውስተ ኢየሩሳሌም ወአኃዝዎ ለስምዖን ወሤምዎ ኤጲስ ቆጶሰ በውስተኢየሩሳሌም። ወነበረ እንዘ ይሜህሮሙ

ባሉ በዚህ ሕዝብ ሁሉ ፊት በተቀደሰው ስምህ ያምኑ ዘንድ አለ።

8. የተባረከው ሐዋርያ ይህን በተናገረ ጊዜም ጉልማሳው ወደ አለበት ቦታ ፊቱን መለሰ። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተነሥና ቁም፤ ከዚህ የተሰበሰቡት ሁሉ ምስጋና ይግባውና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያምኑ ዘንድ አለ። በዚያችን ሰዓትም የዚያህ ጉልማሳ ዓይን ተከፈተ። ተነሥቶም ሄደ። የሚበላውን ያመጡለት ዘንድም አዘዘ።

9. የተሰበሰቡት ሰዎች ይህን በተመለከቱ ጊዜም ሁሉም ወደ መሬት ዝቅ ብለው ለሐዋርያው ሰገዱለት። ሁሉም በእግዚአብሔር አመኑ። እርሱም ምስጋና ይግባውና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው የሚሆን የስምዖን አምላክ እግዚአብሔር አንድ ነው የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው አላቸው። የጉልማሳው አባትም አመነ። ሁሉም ለተቀደሰው ሐዋርያ ሰገዱ። አቤቱ ሆይ በምን እንድናለን አሉት። እናንተ በፍጹም ልባችሁ እመኑ ትድናላችሁም አላቸው።

10. እርሱም ቅዱሳት መጻሕፍትን አስተማ ራቸው። በሀገር የሚኖሩትንም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቃቸው። ሥጋውንና ደሙንም አቀበላቸው። ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩም አዘዛቸው። ለተሰበሰቡት አለቃ የሚሆን ስሙ ቆርነሌዎስ የሚባል ኤጲስ ቆጶስም ሾመላቸው። ቀሳውቱንና ዲያቆናቱንም ሾመላቸው። ቅዱስ ወንጌልንም ሰጣቸው። የእግዚአብሔርን ሕግ እያስተማራቸውም ለሠላሳ ቀን ያህል ተቀመጠ። ከዚህ በኋላም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

11. አይሁድቅዱስ ያዕቆብን በገደሉት ጊዜም ደቀ መዛሙርቱ በኢየሩሳሌም ነበሩ። ስምዖንንም ያዙትና በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስነት ሾሙት። የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተምራቸውም ኖረ።

ቃለ እግዚአብሔር ወይነግሮሙ ዘውስተ ወንጌል ወድኅነት ነፍሳቲሆሙ፤ ወአይሁድኒ እንዘ ይትመዓዑ ላዕሌሁ ውስተ ኢየሩሳሌም እንዘ ይሴብሖ ለእግዚአብሔር እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎቱ ስብሐት። በኵሉ ሰዓት ወበኵሉ መዋዕል ለዓለመ ዓለም አሜን።

በወንጌል ያለውንም ስለነፍሳቸው ድኅነት ነገራቸው። አይሁድ በኢየሩሳሌም ሲቆጡትም እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር። በሁሉም ሰዓት በሁሉም ዘመን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን።